# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ኃይል ጫኝ እና አውራጁ ክፍል

ኢያሱ መሰለ

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የሰው ኃይሉን እያበቃ በራሱ አቅም በሚያከናውናቸው ተግባራት ተጠቃሽ መሆን የሚችሉ ውጤቶችን አስመዝግቧል።

ከነዚህም አንዱ በግልገል ጊቤ 2 ኃይል ማመንጫ ጣቢያ የተከናወነው የጥገና ሥራ ነው። በኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች የጥገና ዘርፍ ያለ ኦፕሬሽን ዘርፍ፤ የኦፕሬሽን ዘርፍም ያለ ጥገና ዘርፍ ሕልውና የማግኘታቸው ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ የገባ ነው።

ሁሉም ዘርፎች እርስ በእርስ ተናቦና ተደጋግፎ የመሥራት ተልዕኮ ያላቸው ናቸው። ስለዚህ አንዳንዴ በተናጠል አንዳንዴም በጥምረት ልንገልጻቸው እንችላለን። ከዚህ አንጻር ባለፈው ጽfhፋችን ስለ ጣቢያው የጥገና ዘርፍ ዋና ዋና ተግባራት አንጂነር አሸናፊ የሰጡንን መረጃ ተንተርሰን ማስነበባችን ይታወሳል። በዛሬው ጽfhፋችን ደግሞ ስለጣቢያው የኦፕሬሽን ክፍል ልናስነብባችሁ ወድደናል።

ኢንጂነር ሽመልስ አዱኛ በግልገል ጊቤ 2 ኃይል ማመንጫ ጣቢያ የኦፕሬሽን ክፍል ኃላፊ እንደሚያስረዱት ፤ በኦፕሬሽን ክፍል ለ24 ሰዓታት የማሽኖቹን ሁኔታ እና ከሲስተሞች ጋር የተያያዙ ነገሮችን የመቆጣጠርና የመከታተል ሥራ ይሠራል። ከብሔራዊ የኃይል ቋት ጋር በመናበብ ማሽኖችን ማስነሳት፣ የሚፈለግባቸውን የመጫን አቅም መጫን፣ መቀነስ፣ መቆም ካላባቸውም እንዲቆሙ የማድረግ ተግባራት ይከናወናሉ።

በተጨማሪም ሲስተሙ እንዳይረበሽ የሲስተሙን ቮልቴጅ የተመጣጠነ ለማድረግ የጀኔሬተር ቮልቴጆችን የመጨመር ወይም የመቀነስ ሥራ ይሠራል። በማሽኖቹ አጠቃላይ ሲስተም ላይ ክትትል በማድረግ እያንዳንዱ ንዑስ ሲስተም (Sub Systems ) የሚጠበቅበትን



ኢንጂነር ሽመልስ አዱኛ

አገልግሎት ለማሽኑ እየሰጠ ስለመሆኑ በየሰዓቱ ይረጋገጣል።

በተጨማሪም በየቀኑ የሚሠሩ የኢንስፔክሽን ሥራዎች አሉ። የባትሪ፣ የኃይል ፣የትራንስፎርመር፣ የኢመርጀንሲ ዲዝል ጀነሬተር፣ እንደዚሁም በስዊችያርድ ላይ በምልከታ ቁጥጥር ይደረጋል። እነዚህ ዘወትር የሚሠሩ ሥራዎች ናቸው፡፡፡

አምስት አምስት አባላት ያሏቸው አራት ቡድኖች በስምንት ሰዓት ልዩነት እየተቀያየሩ ይህንን ተግባር ያከናውናሉ። የኤሌክቲሪካል፣ የመካኒካል ወይም የቴክኒሻንነት ሙያ ያላቸው እነዚህ ሠራተኞች ጀማሪና ልምድ ያላቸው በሚል ከተለዩ በኋላ ተሰባጥረው ይመደባሉ፡፡

እንደኢንጂነር ሽመልስ ማብራሪያ፤ ብልሽቶችን ቶሎ ተረድቶ ፈጣን ምላሽ ካልተሰጠ ችግሮች ሊባባሱ ይችላሉ። ድምፅን በመስማት ብቻ ችግሩ ምን እንደሆነ መረዳት የሚችሉ ሙያተኞች አሉ፤ እነዚህን ሙያተኞች ልምድ ከሌላቸው ጋር እያቀናጁ ማሰማራት ለችግሮች አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችልና ልምድ ለመለዋወጥም የሚያግዝ ነው።

እያንዳንዱ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ሥራውን የሚያከናውነው ከብሔራዊ የኃይል ቋት በሚመጣ ትእዛዝ መሠረት ነው። ብሔራዊ የኃይል ቋት አጠቃላይ የሀገሪቱን የኃይል አጠቃቀም ሁኔታ የሚከታተልና የሚቆጣጠር እንደመሆኑ ተጨማሪ ኃይል ተጠቃሚ ሲገባ ወይም ሲወጣ እየተከታተለ እንደየጣቢያዎቹ አቅም ኃይል እንዲጨመር ወይም እንዲቀንስ ትዕዛዝ ያስተላልፋል። የኦፕሬሽን ባለሙያዎችም በትዕዛዙ መሠረት ምላሽ ይሠጣሉ።

አንዳንድ ጣቢያዎች በጥገና ምክንያት ሥራ ሲያቆሙ የኃይል እጥረት እንዳይከሰት ሌሎች ጣቢያዎች ያንን የሚያካክስ ኃይል እንዲጨምሩ የሚያስገድድ ሁኔታም ሊፈጠር ይችላል። በዚህ መንገድ እየተናበቡና ትዕዛዞች ተፈጻሚ እየተደረጉ የኃይል አቅርቦቱ ከተጠቃሚው አንጻር እየተመጣጠነ እንዲሄድ ይደረጋል ይላሉ ኢንጂነር ሽመልስ።

ኃይል ለማመንጨት ወሳኝ ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ የውሃ አቅም ነው። ግልገል ጊቤ 2 ለየት ከሚያደርጉት ነገሮች ደግሞ የራሱን ግድብ የማይጠቀም መሆኑ ነው። ይሁንና ከግልገል ጊቤ1 ኃይል አመንጭቶ የሚወጣውን ውሃ አንድ ቦታ አቁሮ የሚይዝ አነስተኛ የውሃ ማጠራቀሚያ ቦታ አለው። የውሃውን መጠን የሚለኩና ከኦፕሬሽን ክፍል ጋር በየጊዜው የሚናበቡ ሠራተኞችም በሥፍራው አሉ። የውሃውን መጠን ሲያሳውቁ በዚያው መሠረት ምን ያህል ኃይል እያመረትን እንጓዝ የሚለውን ለመወሰን ይረዳል። የውሃው መጠን የሚመረተውን ኃይል ለመቀነስም ይሁን ለመጨመር አንዱ መነሻ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ምናልባት ጊቤ 1 በጥገና ወይም በሌላ አጋጣሚ ኃይል ማመንጨት ቢያቆምና ወደ ጊቤ 2 የውሃ ማጠራቀሚያ የሚለቀቅ ውሃ ባይኖር ጊቤ 2 የጊቤ 1 ችግር እስከሚቀረፍ መጠነኛ ውሃ ብቻ ተጠቅሞ መጠነኛ ኃይል እያመረተ ይቆያል። የጊቤ አንድ ችግር በፍጥነት የማይፈታ ከሆነ ግን በውሃ ማስተንፈሻው <<Bottom Outlet>> አማካኝነት ውሃ እየተለቀቀለት ወደ መደበኛ ኃይል የማመንጨት ተግባሩ ይገባል።

አንድ ማሽን የተለያዩ ሲስተሞች አሉት በጊቤ 2 በተደጋጋሚ የሚያጋጥመው ችግር ማቀዝቀዣው ፓንፕ<<Primarly Cooling pump>> ነው። ይህ ሲስተም ዋና ተግባሩ ማሽንን ማቀዝቀዝ ነው። በተለይም በክረምት ጊዜ ደለልና አሸዋ ስለሚገባበት ለብልሽት የተጋለጠ ነው። አንድ ኦፕሬተር የማቀዝቀዣ ፓንፑ ችግር እንዳጋጠመው ከተረዳ መጀመሪያ ማድረግ የሚገባው ቀስ ብሎ እያቀዘቀዘ ማሽኑን አቁሞ ለኦፕሬሽን ክፍል ኃላፊው ማሳወቅ ነው። ኦፕሬሽን ክፍሉ መረጃዎችን በደንብ ካጠናቀረ በኋላ ለጥገና ክፍሉ ያሳውቃል። የጥገና ክፍሉ ችግሩ ኤሌክትሪካል ነው ወይስ ሜካኒካል የሚለውን ካወቀ በኋላ ወደ ጥገና ሥራው ይገባል ማለት ነው። ለምሳሌ ብልሽቱ መካኒካል ከሆነ የተበላሸውን እቃ አውጥቶ ተጠግነው የተቀመጡ የመለዋወጫ እቃዎችን በመግጠም ማሽኑ ወደ ሥራው እንዲገባ ያደረጋል።

የጥገና ሥራው ከመጀመሩ በፊት ለብሔራዊ የኃይል ቋት ማሳወቅ የግድ ይላል። ጊቤ 2 በኖዝሎች ላይ ጥገና አድርጎ ኃይል የማመንጨት አቅማቸው የቀነሰ ተርባይኖች ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ የተደረገውም በዚህ ሂደት ነው።

‹‹በግልገል ጊቤ 2 ኃይል ማመንጫ ጣቢያ የኦፕሬሽን እና የጥገና ሠራተኞች ሥራዎችን ተጋግዘው ይሠራሉ። የኦፕሬሽን ሙያተኞችን ሥራ የጥገና ባለሙያዎች፤ የጥገና ሙያተኞችን ሥራ የኦፕሬሽን ሠራተኞች በትብብር የሚሠሩበት የሥራ ባሕልም ዳብሯል። ይህም ለውጤት አብቅቶናል›› ይላሉ ኢንጂነር ሽመልስ።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ